ፓኖራማ ቁጥር 52

የትዝብት አድማስ

ኅዳር 19 ቀን 2001 ዓም

## ኢትዮጵያን ለማጥፋት የውጭ ኃይሎች ምን ሚና ተጫውተዋል?

ሀገራችን ኢትዮጵያ አሁን ከደረሰችበት ጨርሶ የመጥፋት አደጋ ላይ እንድትወድቅ ያበቋት በአመዛኙ የውስጥ ኃይሎች የመሆናቸው ጉዳይ በአሁኑ ወቅት ከሞላ ጎደል ያልተረዳው ማንም ኢትዮጵያዊ ሊኖር አይችልም። ችግሩ ግን ኢትዮጵያዊ ሁሉ ሀገሩ እዚህ ደረጃ እንድትደርስ ያበቋትን እነዚህን ምክንያቶችና ተዋናያን በአሁኑ ወቅት የማወቅና ያለማወቅ ጉዳይ አይደለም። ይልቁንም፥ያለፈው ሁኔታ ተመልሶ እንዳይደገም አሁንስ ምን እየተደረገ ነው? የሚለውን ጥያቄ በበቂና በአስተማማኝ ደረጃ መልሶ መፍትሄውን ከመፈለጉ ላይ ነው። ይህንን ለማለት ያስቻለን፥ካለፈው ታሪኩ የማይማር ሕዝብ፥ ተመሳሳይ ስህተት በመፈፀም የሚረገም እንደሚሆን ለማስመዝገብ ነው።

በአስራ ስድስተኛው ክፍለ ዘመን የወቅቱ የዓለም ኃያላን የነበሩት የኦቶማን ተስፋፊ አገዛዝና የፖርቱጋል ቅኝ ገዢ መንግሥት ለግዛት ማስፋፋት፥ ለጥሬ ሀብት ማካበትና ለሸቀጣቸው ዕቃ ማራገፊያ ሲሉ ባደረጉት የየግላቸው መራኮት፥ ኢትዮጵያን የመራኮቻቸው መድረክና የመስፈንጠሪያ መድረክ በማድረግ በሀገራችን ላይ ያስከተሉትን ብሄራዊ ጥፋት እንደ ማስረጃ ጠቅሶ ከማለፍ በስተቀር በታሪክ የተመዘገበ ስለሆነ ወደ ዝርዝር ጉዳዩ መግባት አስፈላጊ ሆኖ አላገኘነውም። በሀያኛው ምዕተ ዓመት ማክተሚያ ደግሞ አሜሪካና የቀድሞዋ የሶቬየት ኅብረት ለራሳቸው ጥቅም ሲሉ ሀገራችንን ለጥቅማቸው ማስፈፀሚያ አገልጋይ ለማድረግ አሁን ለምትገኝበት አሳዛኝ ሁኔታ ከፍተኛውን ሚና ተጫውተዋል። በሌላ በኩል ግን ሁል ጊዜ ለችግራችን

ምክንያት ሁሉ የውጭን ኃይላት እንደሰበብ ለመቁጠር በምናደርገው ማጠየቂያ ሲባል የማስረጃውን ዝርዝር ማስረዘም የሚጠቅም አይሆንም። እኛስ እንደ ሕዝብ ሁኔታው እንዳይፈጠር ምን እያደረግን ነበር?ዛሬስ ቢሆን የመከላከያ ርምጃስ እያደረግን ነው ወይ? ብለን መጠየቅ ይገባናል።
ለዚህ ጥያቄ የምናገኘው መልስ፥ ሁሉም ክፍል አሁን ላለው ሁኔታ የየራሱን አስተዋፅኦ አድርጓል ከማለት ሌላ መልስ የሚገኝለት አይመስለንም። ለአንድ ሀገር ሕዝብ የቅድሚያ ትኩረቱና ግዴታው ሀገሩን የሚያጠፉትን የውጭ ጠላቶችም ይሆን የውስጥ ከሀዲዎች መቋቋምና ማጥፋት ለመሆኑ፥ ለኢትዮጵያ ሕዝብ መንገር ድፍረት መሆኑን ብንረዳም፥የውስጥ ባንዳዎችና የውጭ ጠላቶች ተባብረው ሀገራችንን ሲያጠፏት ያመረቃ ተግባር ባለማከናወናችንና አይበገሬነትን ባለመሳየታችን፥ማንንም ልንወቅስና ልናማርር የሚገባን አይሆንም ።
ለጊዜው በእኛ በኩል ከንዝህላልነትና ከተለያዩ ምክንያቶችም ጭምር፥ ሳይደረጉ የቀሩትን ሀገርን ከጥፋት ለመከላከል ሊወሰዱ የሚገባቸውን ርምጃዎች ለጊዜው ወደኋላ አስቀርተን፥ በቅርቡ፥ባዕዳን በሀገራችን ላይ የተረባረቡትን ደባና ጥቃት ማስመዝገብን እንሻለን። ይህንን ማድረጋችን፥ ለኋላው ጊዜ "ይህንን ተናግረን ነበር፥ ይህንንም አስመዝግበን ነበር፥ የሚሰማን አጥተን ነው እንጅ" እያልን ከታሪክ ወቀሳ ነፃ ነን የሚለውን የከንቱ ውዳሴና የሥነ- አዕምሮ ዕፎይታ ለማግኘት አይደለም። ታሪክ ሁሉንም እንደ ምግባሩና ተግባሩ ሊገመግምና ሊፈርድ ስለሚችል ፥ያ ጉዳይ እኛን አያስጨንቀንም። ሰብዓዊ ፍጡር ሁሉ ሊጨነቅና ሊጠበብ የሚገባው፥የጎሊና ወቀሳ እንዳያጋጥመው እንጅ፥ ማንም ምን ይሁን ለሚያደርገው የጥላቻና የቂም በቀል ዛቻና ማስፈራራት አይደለም።

ሁሉም ኢትዮጵያዊ/ት በትክክል እንደሚረዳው፥ባዕዳን ከጥንት ጀምሮ፥ በተለያዩ ምክንያቶች በሀገራችን የውስጥና የውጭ ጉዳዮች ጣልቃ እየገቡ ለነፃነታችን ብቻ ሳይሆን ለመሠረታዊ ህልውናችንም እንኳ ሳይቀር ችግር ፈጣሪዎች ነበሩ። በኢትዮጵያ ላይ ዘመን የማይሽረው ይኸን ያህል ትኩረት

ሊደርጉ የቻሉበት ምክንያት በየጊዜው ተደጋግሞ የተመዘገበ በመሆኑ፥ ያንን ማንሳት፥ ማስለቸት ስለሚሆን ወደ ዝርዝር ጉዳዮቹ መግባት አስፈላጊ ባይሆንም፥ ዋና ዋናውን ግን መዳሰስ የሚከፋ አይደልም፡፡ ለዚህ ሀተታ መነሻ የሆነን በዘመነ ደርግ  በኢትዮጵያ ሀገራችን ላይ የተፈፀመው የባዕዳን የተቀነባበረ ሴራ እንዴት አድርጎ ሀገራችንን አሁን ካለችበት የጥፋት ጠርዝ ሊያደርሳት እንደበቃ ነው፡፡ ለዚህ የጥፋት አዝማጆች  የነበሩት የሁለቱ ኃያላን መንግሥታት የስለላ ድርጅቶች ግንባር ቀደም ሚና ተጫውተዋል፡፡ የቀድሞዋ የሶቬየት ኅብረት ኬጂቢና የአሜሪካው ሲ አይ ኤ መሆናቸው ነው፡ “ ሁለት ዝሆኖች ሲፋተጉ ሳሩ ይደቃል” እንደሚባለው፥ሁለቱም ለየራሳቸው ምክንያቶችና ጥቅሞች ሲሉ ሀገራችንን ለመስዋዕት ጠቦት በማቅረብ ተበታትና ተፈረካክሳ እንድትቀር የየበኩላቸውን ሚና ተጫውተዋል፡፡በተለይማ የአሚሪካው የስለላ ተቋም፥ በኢትዮጵያ የመከላካያ ሠራዊትና በሀገራችን ልዩ ልዩ ተቋማት ውስጥ ሰርስሮ በመግባት ግዙፍ የነበረውን ሠራዊትና የመካላከያ ተቋም ብትንትኑን እንዲወጣ አድርጎታል፡፡

ሀገራችን በውስጥ ባንዳ ከሃዲዎችና በውጭ ጠላቶች ትብብር ሦስተኛው ዓለም ተብለው ከተመደቡት ሕዝቦች የመጨረሻውን ደረጃ ይዛ እንድትገኝ ሆናለች፡፡ የዛሬ አምሳና ስድሳ ዓመታት አካባቢ ከኢትዮጵያ ጋር በተመሳሳይ ደረጃ የነበሩ ሀገሮች ዛሬ  በሁለንተናዊ መስፈርቶች በተሻለ ሁኔታ ላይ የሚገኙ ሲሆኑ፥ ኢትዮጵያ ግን በአሁኑ ወቅት የነርሱ መፅዋች ሁናለች፡፡ ኃያላኑ የኢትዮጵያን መጠንከር፥ ዕድገትና ታላቅ መሆኗን ስለማይፈልጉ፥በአፍሪካ ቀንድም ይሁን በቀይ ባህር አካባቢ  ጠንካራዋን ሀገርና ኃያሏን ኢትዮጵያ ማየት ቀርቶ መስማትን አልፈለጉም/አይፈልጉምም፡፡ይህንን ዕቅዳቸውን ተግባራዊ ለማድረግ አመች ጊዜና  ተስማሚ ሁኔታን ለማምጣት አድፍጠው ሲሸርቡ ቆይተው ሰኔና ሰኞ ሲገጣጠሙላቸው ምኞታቸውን  አሳክተዋል፡፡ ይህም አሁን ሀገራችን ያለችበትን ሁለንተናዊ ክስተት አስከትሏል፡፡ በደርግ ዘመን የተደራጀውን የመከላካያ ሠራዊት እንዳልነበር ለማድረግ ግንባር ቀደሙን ሚና የተጫወቱት ያሜሪካ ወታደራዊ ባለሥልጣኖችና የስለላ መረባቸው እንደነበሩ የሚያከራክር

አልነበረም:: ዛሬ ይህንን ኃሳብ የሚያዳምጡ ወኪሎቻቸው፥" ጅብ ከሄደ ውሻ ጮኸ" በሚል ምፀት እራሳቸውን ሊያፅናኑ ቢከጅሉም፥ኢትዮጵያ ሀገራችን ግን " የወጋ ቢረሳ፥የተወጋ አይረሳ" በማለት ከወደቀችበት ትቢያ በራሷና በቆራጥ ልጆቿ መስዋዕት ህልውናዋን፥ነፃነቷንና የዜጎቿንም አንድነት አስከብራ ትንሳዔ ሙታንን እንደምታመጣ ማንም ሊጠራጥር አይችልም:: ይህንን ክስተት ለማግኘት ግን በደርግ የመጨረሻ ሁለት ዓመታት በሀገራችን የተከናወኑትን ደባዎች ባጭሩም ቢሆን መዳሰስ የሚያስፈልግ ይሆናል:: ይህም ለወደፊቱ የሀገር ማዳን ትግል የሚረዳ ተመክሮ ይለግሳል ከሚል ዕምነት ነው::

በአሜሪካና በቀድሞዋ የሶቬየት ኅብረት መሃል በነበረው የፖለቲካ፥ የወታደራዊ፥ የምጣኔ ሃብትና የሥነ ልቦና ፍትጊያ በፈጠረው ውጥረት፥ በወቅቱ የሲቭየቶቹ መሪ የነበረው ሚካሄል ጎርቫቾቭ ባወጣው የፔረስትሮይካ መርኅ መሠረት በተከሰተው የቀዝቃዛው ጦርነት ለውጥ ምክንያት፥ የሶቬየቱ ጎራ ባልተጠበቀ ፍጥነት እንደ እምቧይ ካብ እየተናደ ሄደ:: ይህ ክስተት ለአሜሪካን አፄአዊ ሥርዓት " ላሜ ወለደችልኝ" ሆነለት:: ይህ ክስተት አሜሪካ የዓለምን ሁኔታ በብቸኝነት እንድትቆጣጠረው የሚያስችላትን አጋጣሚ አመቻቸላት::ሶቭየት ህብረትንም ከስር መንግሎ ለመጣል ያልተጠበቀ ምቹ ሁኔታን ፈጠረላት:: የሶቭየት ጋሻ ጃግሬ የነበሩት ሀገሮች የአሜሪካ ሰለባዎች ሆኑ:: በደርግ አምባገነን ስር የነበረችዋ ሀገራችንም የዚህ ሰለባ ከመሆን አልዳነችም::ደርግና አማካሪዎቹ ይህንን ሁኔታ ተገንዝበው በወቅቱ፥ሀገር የሚድንበትን ብልሃትና መከላካያ እንደማዘጋጀትና ብሎም በኢትዮጵያ መሠረታዊ ጠላቶች ላይ ማተኮር ሲገባቸው፥ጭራሹኑ ኢትዮጵያን ከተቃጣባት አደጋ ለመታደግ ሲፋለሙ የነበሩትን ሀገር ወዳድ ተጋዮች ማጥቃቱንና ማጥፋቱን ቀጠሉበት::በመጨረሻው ሰዓትም ሁኔታዎች እየተባባሱ ሲመጡ እንደ ተደገመበት ጋኔል ደንዝዘውና እንደ ተተኮሰበት ድኩላ ፈዝዘው ቀሩ::ይህንን ሁኔታ በትክክል የተገነዘበው የአሜሪካ የስለላ ማዕከል ( ሲ. አይ. ኤ)፥ ለአያሌ ዓመታት በምሥጢር ሲሰራበት የቆየውን የመረጃ ክምችት

በመጠቀም የአሜሪካንን ስትራተጂያዊ ጥቅም ይፃረራሉ የሚሏቸውን፥ የሱዳንንና የኢትዮንና መሪዎች ለማስገልበጥ ወሰኑ። ይህንን ለማሳካት ሁለት የተለያዩ የመንግሥት ግልበጣ ሴራዎች ተጠነሰሱ። የሱዳኑ ሲሳካ የኢትዮጵያው ከሸፈ። በኢትዮጵያው ሙከራ ስንት ታዋቂ የጦር መኮንኖች አለቁ። ያን የመሰለ የኢትዮጵያ የመከላካያ ሠራዊት ያለ መሪ ቀረ። ለሻዕቢያና ለወያኔ የወታደራዊ መረጃ በማቀበል የኢትዮጵያ ሠራዊት እንዲጠቃ አደረገ። በወያኔና በሻዕቢያ መካከል ሻክሮ የቆየውን ግንኙነት አለስልሶ ሁለቱም እንዲስማሙ አደረገ። ለዚህም ወሳኝ ሚና የተጫወተው የቀድሞው የአሜሪካ ፕሬዝደንት የነበረው የኢትዮጵያ ጠላት ጂሚ ካርተርና በአፍሪካ ቀንድ የአሜሪካ የመረጃ ኃላፊ የነበረው ሪቻርድ ፈን ዳላስ ነበሩ። አሜሪካ በዳህላክ ደሴቶች ሰፍሮ የነበረውን የሶቬየት ኅብረትን የጦር ኃይል ለመቀናቀንና ከአካባቢው ለቅቆ እንዲወጣ በነበረው ብርቱ ፍላጎት ፥ሁለቱንም የሽምቅ ተዋጊዎች በበለጠ ለመርዳት በገባው ቃል መሠረት፥ የአሜሪካ የስለላ ማዕከል፥ አስፈላጊና ጠቃሚ የሆኑትን ወታደረዊ መረጃዎችን በመስጠት፥ ኤርትራ ውስጥ አፍዓባት ላይ ሰፍሮ የነበረውን ሠራዊት ሻኣቢያ እንዲያጠቃ ሲያደርግ፥በትግራይ ክፍለ ሀገር ደግሞ፥ሽሬ አውራጃ ውስጥ እንዳባጉና ላይ ሰፍሮ ዘመናዊ የስለላ መሣሪያዎች ታጥቆ በነበረው ሠራዊት ላይም ወያኔ አመርቂ ጥቃት እንዲፈፅም አስችሎታል። ወያኔም ወደ አዲስ አበባ በመሄድ ደርግን በማስወገድ የአሜሪካን አሻንጉሊት ቡድን ለመትከል የመጨረሻውን ቡራኪ የሰጠው የቀድሞው የአሜሪካ ፕሬዝዴንት የነበረው ሚስተር ቡሽ ነው። ከአሜሪካኖች በተለገሰላቸው ወታደራዊና ፖለቲካዊ መረጃ መሠረት፥በበርካ ሚሊዮን ሀብት የተደራጀ፥በዘመናዊ መሣሪያ የታጠቀና የሠለጠነ የኢትዮጵያ የመከላከያ ሠራዊት፥ በከሸፈው በግንቦቱ መፈንቅለ መንግሥት ምክንያት ብቃት የነበራቸውን ሀገር ወዳድ ጀኔራል መኮንኖችና ወታደራዊ መሪዎች በማጣቱ በቀላሉ ሊያጠቁት ችለዋል።ከዚህ ደባ በኋላ፥ኮሎኔል መንግሥቱ ሠራዊቱን በመበተን ሀገሪቱንም አጋልጦ ጠፍቶ ሲሄድ፥ በአሜሪካው የስለላ ማዕከል በኩል

የተሰጠውን የቤት ሥራ አድፍጦ በሚገባ ሲያከናውን በነበረው በሂርማ ኮኸን አማካኝነት ሎንዶን ላይ በተጠረውና የኢትዮጵያንም ሀገራዊ ጥቅም ለመወከል ባልታሰበበት ስብሰባ  የውጭ ኃይሎች ያዘጋጁት ሀገራችንን የማጥፋት ደራማ ተፈፀመ፡፡ በደርግ ውስጥ ባለሥልጣን የነበሩት ከተስፋዬ ወልደ ሥላሴ ጀምሮ እነ አሻግሬ ይግለጡና ሌሎችም የሲአይኤ ቅጥረኞች ሆነው ማገልገላቸው ደግሞ ዛሬ ምስጢር አይደለም፡፡ ከዚያ በኋላ ያለውን ሂደትና ክስተት ማንሳቱ በሌላ  የታሪክ  ምዕራፍ ታሪክ ራሱ ይመዝገበው እንጅ ለአሁኑ ወቅት ትኩረታችንን አናሳርፍበትም፡፡

ብቻ አንድ አንድ ግንዛቤዎችን ለወደፊቱ ርምጃችን ይጠቅሙ የሆናል በሚል ማስፈርን እንሻለን፡፡

1. ከላይ የተዘረዘሩት ሀገራችንን የማጥፋት ደባዎች ሲፈፀሙ፥ ማንም የውጭ ኃይልም ይሁን የሀገር ውስጥ ተቆርቋሪ  በኢትዮጵያ በኩል አለመቆሙን፥ ይህም ምን ጊዜም ቢሆን ሀገራችን በመከራዋ ጊዜ ከጎኗ የሚቆምላት ዕኑ የሩቅ ዘመድም ይሁን የቅርብ ወዳጅ እንደሌላት፥

2. ለጉዳትም ይሁን ለጥቅም በሀገራችን እስካሁን ድረስ የተሳካ መፈንቅለ መንግሥት (ኩዴታ)  አለመመዝገቡ፥  የውጭ ሀገር የስለላ ማዕከሎች ለተመሳሳይ ዓላማቸው  በተመሳሳይ ሁኔታ በአዲስ አበባና በካርቱም እንዲፈፀም  ያደረጓቸው፥ ሁለት መፈንቅለ መንግሥቶች (ኩዴታዎች) የሱዳኑ ሲሳካ፥  የኢትዮጵያው አለመሳካቱ፥ እንዲያውም ለሀገር የሚጠቅሙ ምርጥ ጄኔራል መኩንኖች በከንቱ መጨፍጨፋቸውና ሀገሪቱ ሠራዊት ማጣቷ፥ ይልቁንም የመከላከያ ኃይል በጥቅሉ መፈራረሱ፥

3. አሁንም ሀገራችንን በበለጠ ለማጥፋት ስውር ደባዎች በረቀቀ ዘዴ

እየተሸረቡ መሆናቸውን፥ ብሎም ትላንት መንግሥቱ ኃይለማርያምን በመለስ ዜናዊ በመተካት የሚጋልቡት ፈረስ እንደለወጡ ሁሉ፥ ወደፊትም በአዲስ መልክ የሚጋልቡትን አዲስ ታማኝ ፈረስ ሊያዘጋጁ እንደሚችሉ፥

4. ዛሬም እንደትላንቱ በተቃዋሚው ክፍልም ይሁን በምሁራን፥ ወይም በሌሎች የኅብረተሰብ ክፍሎች ዘንድ ያለፈው እንዳይደገምና ሀገራችንን ከዳግም መቅሰፍት ለመከለከል ምንም ዝግጅት ለማድረግ ጥረቱ እንደማይታይ፥
5. ዛሬም እንደ ትላንቱ የሲአይኤ ወይም የባዕድ ቅጥረኞች የፖለቲካው መድረክ ላይ እየተርመሰመሱ መሆናቸውን መገንዘብ እንደሚገባ ለማሳሰብም ነው።

እነዚህ ክስተቶች ሊኖሩ ቢችሉም ቅሉ፥ የማታ የማታ በየጊዜው በባዕዳኑም ይሁን በውስጥ ጠላቶቿ የሚሸረብባትን በመቋቋም ሀገራችን ኢትዮጵያ እንደገና ከወደቀችበት እንደምትነሳ የኢትዮጵያ ሕዝብ አንዳችም ጥርጣሬ አይኖረውም። ንቁ ዜጋ ሆነን መገኘት ግዴታችን የሚሆነውም ለዚህ ነው።